# የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል ሙሌት ስርዓት ረቂቅ መመሪያ ማብራሪያ

## መግቢያ

ከውጭ በሚገቡ ነዳጅ እና የነዳጅ ውጤቶች ላይ ያለውን መተማመን መቀነስ እና የተስፋፋውን የንግድ ሚዛን መዛባት ለመቅረፍ በትራንስፖርት ውስጥ የአገር ውስጥ ታዳሽ የኃይል ሀብቶችን መጠቀም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በተለይም በከተሞች ውስጥ በሰው ልጅ ጤና ላይ ተጽዕኖ በሚያሳድር መልኩ በመንገድ ትራንስፖርት ውስጥ ከነዳጅ አጠቃቀም አኳያ የአየር ብክለትን መቀነስ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ከትራንስፖርት የግሪንሀውስ ጋዝ ልቀት በመቀነስ የኢትዮጵያ የአየር ንብረት ቃል ኪዳንን ለማሟላት አስፈላጊ አካል በመሆኑ፤

ለመንገድ ትራንስፖርት የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ስራ ላይ ለማዋል ከላይ የተጠቀሱትን ተግዳሮቶች ለመቅረፍ አስተዋፅዖ የሚያደርግ ሲሆን የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን ሰፋ ባለ መልኩ በማስገባት በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ ስርዓቶች መኖር እና ተደራሽነት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፤

በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ  የሃይል ሙሌት መሰረተ- ልማት ተከላ እና አገልግሎት ንግድ ላይ ለመሰማራት ለሚፈልጉ ዝቅተኛ የፈቃድ መስፈርቶችን እና ደረጃን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ  የሃይል ሙሌት ጣቢያዎች እና ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባለቤቶች ተመጣጣኝ የሃይል ሙሌት ታሪፍ ተመን ማውጣት በማስፈለጉ፤

የነዳጅ እና ኢነርጂ ባለስልጣን በአዋጅ ቁጥር 810/2006 አንቀጽ 40(2) እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢነርጂ ደንብ ቁጥር 447/2011 አንቀፅ 82 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል ሙሌት ስርዓት መመሪያ ተዘጋጅቶ ለዉሳኔ ቀርቧል፡፡

ይህ ረቂቅ መመሪያ ሲዘጋጅ አዲስ ዘርፍ ከመሆኑ አንፃር ጉዳዩን በመመርመር፣የቁጥጥር ስራዉን በማሻሻል የዘርፉን ልማት እንዲያሳድግ ታስቧል፡፡ በዚሁ መሠረት ረቂቅ መመሪያዉ 7 ክፍሎች ፣ 22 አንቀጾች  እና ሁለት አባሪዎች ያሉት ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

## የዋና ዋና ክፍሎች ማብራርያ

1. **<u>ክፍል አንድ</u>** አንቀጽ 1 ፣2 እና 3 ፡- አዉጪዉ ባለሥልጣን ፣አጭር ርዕስ እና ትርጓሜን የያዘ ሲሆን ፣
   - <u>አዉጪዉ ባለሥልጣን</u> መመሪዉ የተዘጋጀበትን የህግ መሠረት የሚገልፅ ነዉ ፡፡
   - <u>አጭር ርዕስ</u> የደንቡን ስያሜ " የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል ሙሌት ስርዓት መመሪያ " በሚል ተሰይሟል፡፡
   - <u>ትርጓሜ</u> ላይ በመመሪያዉ ዉስጥ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸዉ 16 ቃላት ዝርዝር ትርጉም ተሰጥቷቸዉ በዚህ አንቀጽ ስር ተቀምጠዋል፡፡
2. **ክፍል ሁለት** ከአንቀፅ 4 — 7 ያሉትን የያዘ ሲሆን፣
   1) **<u>አንቀፅ 4 የመመሪያዉን ዓላማ፡-</u>** የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በኢትዮጵያ በፍጥነት ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ደህንነቱ የተረጋገጠ፣አስተማማኝ፣ተመጣጣኝ እና ተደራሽ የኃይል መሙያ መሠረተ-ልማት መኖሩን ለማረጋገጥ ፤ ኦፕሬተሮች/ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ባለቤቶች ተመጣጣኝ የኃይል ሙሌት ታሪፍ/ተመን ለማውጣት እና ለአየር ንብረት ለውጥ እና ለከባቢያዊ አየር ሙቀት ወይም ለካርቦን ልቀት መቀነስ ላይ የበኩሏን አስተዋጽኦ እንድታበረክት ለማድረግ ነው፡፡
   2) አንቀፅ 5 የመመሪያዉን የተፈጻሚነት ወሰን የሚመለከት ሲሆን የኃይል አቅርቦት ምንጩ ከብሔራዊ ግሪድ ወይም ከግሪድ ውጪ ባለ ስርዓት በሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ ለኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ ኃይል ሙሌት አገልግሎት በሚሰጥ ወይም በሚጠቀም ማንኛውም ሰው/ድርጅት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡
   3) አንቀፅ 6 የኤሌክትክ ኃይል መሙያ አገልግሎቶችን እና ዘዴዎችን የሚዘረዝር ሲሆን በሶስት የኃይል ሙሌት አገልግሎቶች ማለትም በቤት ፣ የህዝብ እና ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ወይም ለራስ አገልጎሎት የሚዉሉ ኃይል መሙያ ጣቢያዎች አገልግሎት የሚዘረዝር ነው፡፡ በተጨማሪም ከታች የተዘረዘሩትን አራት የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም የሚያስችል ነው፡፡
      - ዘዴ 1 ምንም አይነት ግንኙነት ወይም የደህንነት ባህሪያትን የማይደግፍ እና የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪን ሙሉ በሙሉ ለመሙላት ወደ 8 -12 ሰዓታት ያህል የሚወሰወድ ዘዴ መሆኑ
      - ዘዴ 2 እንደ ዘዴ 1 ሁኖ ግን ከመጠን በላይ ሙቀትን እና የኤሌክትሪክ ንዝረትን ለመከላከል በኬብል ቁጥጥር እና ጥበቃ መሣሪያ (አይሲ-ሲፒዲ)ባለው ልዩ ገመድ የተጠበቀ መሆኑ፣

- ዘዴ 3 ከፊል ፈጣን ዘዴ ሁኖ የሀይል ፈሰትን እና ቮልቴጅን የሚያስተካክል ራሱን የወሰነ የግድግዳ ሳጥን  የሚጠቀም መሆኑ፣
- ዘዴ 4 ደግሞ  ፈጣን የዲሲ መሙያ ጣቢያ በመጠቀም የኤሌክትሪክ ተሸከርካሪ ቦርድ ቻርጀርን የሚያልፍ እና ባትሪውን በቀጥታ የሚሞላ የሚደነግጉ ንኡስ አንቀጾች የያዘ ነው፡፡

3. **ክፍል ሶሥት አጠቃላይ አቅርቦት**

- አንቀጽ 7 አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ኃይል ሙሌት መስፈርቶችን የያዘ ሲሆን በስሩ 20 ንኡስ አንቀጾች የያዘ ሁኖ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የኃይል መሙያ ጣቢያዎች ሁሉንም የሚመለከታቸውን ብሔራዊ፣ የክልል እና የአካባቢ ህጎችን ፣ ደንቦችን ፣ ደረጃዎችን እና ኮዶችን በተጨማሪም ከኤሌክትሪክ ደህንነት ፣ ከእሳት ደህንነት ፣ ከአካባቢ ጥበቃ እና ተደራሽነት ጋር የተዛመዱትን ማክበር እንዳለባቸው የሚደነግግ ነው፡፡፣

4. **ክፍል አራት**  ቴክኒካል ስታንዳርዶች እና ተዛማች መስፈርቶች የሚዘረዝር ሲሆን በስሩ ከአንቀፅ 8 — 15 የያዘ ነው

- አንቀፅ 8  የህዝብ ሃይል መሙያ መሰረተ ልማት መስፈርቶች ፡- ማንኛውም የህዝብ ሃይል መሙያ ጣቢያ  ማሟላት ያለበትን የመሰረተ ልማት መስፈርቶች የሚያስቀምጥ ሁኖ ድህንነት በተመለከተ የኤሌክትሪክ ማሰራጫ ግሪድ ኮድ (የኢትዮጵያ ብሄራዊ ኤሌክትሪክ ማሰራጫ ግሪድ ኮድ) ድንጋጌዎችን ያከበረ መሆን እንዳለበት ፣ የብቻ ትራንስፎርመር ሊኖረው እንደሚገባ ፣ የሕዝብ የኃይል መሙያ ጣቢያዎች በትንሹ ሁለት መሙያዎች ሊኖሩት እንደሚገባ  እና በቂ የሃይል መሙያ ቦታ እና የተሽከርካሪዎች መግቢያ/ መውጫን ጨምሮ ሚሟላት እንዳለበት የሚደነግግ ነው፤
- አንቀፅ 9 የአቅርቦት እና የደህንነት መስፈርቶች  ፡- በዚህ  አንቀጽ የሃይል ሙሌት አቅርቦት ሰርኪዩት ጫፍ ፣ መጠቀም ያለበትን የሰርኪውት መከላከያ መሳርያዎች ዓይነቶች ፣ የኤሌክትሪክ ዝርጋታው የግራውንዲንግ ሁኔታ  ፣ አገናኝ እና አዳብተሮች መከተል ያለባቸውን የአይ ፒኤክስ ኢንዴክሶች ፣ የማስፋፍያ ክፍል ፣ የፍተሻ ምስክር ወረቀት ዓይነት(የአይ.ኢ.ሲ. ስታንዳርዶች) እና  ለህዝብ ተደራሽነት እና ለንግድ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሃይል ሙሌት አገልግሎት ዝርጋታ መስፈርቶች የሚዘረዝር አንቀጽ ነው፡፡

- አንቀፅ 10 የህዝብ እና ለንግድ ላልሆነ ለራስ አገልግሎት ሃይል መሙያ ጣቢያዎች የቴክኒክ መስፈርቶችን የሚያስቀምጥ ሁኖ በዓለም አቀፍ ደረጃ በአብዛኛዎቹ የተሽከርካሪ አምራቾች በስፋት ጥቅም ላይ የሚውሉ ሲሲኤስ እና ቻዴሞ ጥቅም ሊዉል እንደሚችል እና ማንኛውም ፈጣን/ዝቅተኛ/መካከለኛ የሃይል መሙያ የኢትዮጵያ የደረጃዎች ኢንስቲቲዩት መስፈርቶች በወጣው መሰረት ወይም በአባሪ 1 የተቀመጡት ዓይነቶች ሊኖራቸው እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡
- አንቀፅ 11 የህዝብ የሃይል መሙያ መሠረተ ልማት ለረጅም ርቀት ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች ወይም ከባድ ጭነት ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በተመለከተ ሁለት ሃይል መሙያ ቢያንስ ከ 100ኪሎ ዋት (250-750 ቮልት ወይም ከዚያ በላይ) እያንዳንዳቸው ከተለያየ መለያ (ሲሲኤስ እና ቻድሞ) እና ለየብቻው ማገናኛ ገን (Single connector gun) ያለው ሊሆን እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡
- አንቀፅ 12 የህዝብ የሃይል መሙያ ጣቢያዎች መገኛን የሚገልጽ ሁኖ ዝቅተኛ ርቀትን መሰረት አድርጎ በአውራ ጎዳናዎች/ፍጥነት መንገዶች እና ለረጅም እና ከባድ ጭነት ኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች እንደ አውቶቡሶች/የጭነት መኪናዎች ወዘተ የኤሌክትሪክ ሃይል መሙያ ጣብያዎች መዘጋጀት እንዳለባቸው የሚደነግግ ነው፡፡
- አንቀፅ 13 የኃይል ጥራትን ፡- የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪ የሃይል መሙያ አገልግሎት ስራ ከኃይል ጥራት ማነስ ኤሌክትሪክ ባገናኘለት ኃይል አቅራቢ ተቋም በሚሰጠው የኃይል አቅርቦት አገልግሎት ላይ እንደ ሃርሞንክስ፣ፍሊክር፣ዝቅተኛ ቮልቴጅ ለመሳሰሉ ሁኔታዎች አስተዋጽኦ ማድርግ እንደሌለበት ይደነግጋል፡፡
- አንቀፅ 14 ስለቆጣሪ ሜትር ፡- በዚህ አንቀጽ ቆጣሪዎች መገናኑት ያለባቸው በመጨረሻው ቦታ መገጠም እንዳለበት ፣ የኃይል ፍጆታን በኪሎዋት በሰአት የሚመዘግቡ እና ስማርት ሜትር መሆን እንዳለባቸው ይደነግጋል፡፡
- አንቀፅ 15 የህዝብ የሃይል መሙያ ጣቢያዎችን ስለማደራጀት እና ስለስራው ቅድመ ሁኔታ በዚህ አንቀጽ የሃይል መሙያ ጣቢያ ባለቤቱ የራሱ የሆነ መስመር ዝርጋታ፣ የአሰራር እና የጥገና መመርያ ሊኖረው እንደሚችል ወይም ለዚህ ዓላማ ባለስልጣን መ/ቤቱ በሚያወጣው መመርያ መሰረት ለሰራ እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

**5. ክፍል አምስት የፈቃድ እና ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት**

ከአንቀፅ 16 — 18 ያሉትን የያዘ ሲሆን፣

- አንቀፅ 16 የፈቃድ አይነት እና መደቦች የሚያስቀምጥ ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዘርፉ ሶስት የፈቃድ ዓይነቶች እና ሁለት መደቦች (መደብ I እና II) የፈቃድ መደቦች የያዘ ነዉ ።
- አንቀፅ 17 ስለፈቃድ ማመልከቻ እና ፈቃድ አሰጣጥ ሚሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች የሚያስቀምጥ ሲሆን ባለስልጣኑ ለዚህ ዓላማ ያዘጋጀውን ፎርም ሞልቶ አመልካቹ ከሚከተለው መረጃ ጋር ተያይዞ መቅረብ እንዳለበት ይደነግጋል።
- አንቀፅ 18 ስለፈቃድ ማመልከቻ ልዩ መስፈርቶች፡- በዚህ አንቀጽ በአንቀጽ 17 ከተጠቀሱ አጠቃላይ መስፈርቶች በተጨማሪ ማንኛውም የኤሌክትሪክ ተሸከርካሪ የህዝብ ሃይል መሙያ አገልግሎት ፈቃድ ለማግኘት መሚቀርብበት ግዜ ለታሰበው የሃይል መሙያ አገልግሎት የኤሌክትሪክ አቅርቦት ምንጭ፤ የፕሮጀክት ሳይት ካርታ፤ የሃይል መሙያ አገልግሎቱ አጠቃላይ አቅም በኪዋት/ኬቪኤ/፤ የፕሮጀክቱ የአዋጭነት ጥናት እና ለሃይል መሙያ ተቋሙ የአሠራር መመሪያ ፣ የፀደቀ የሃይል ግዥ ስምምነት(አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ)፣ የፕሮጀክት ፋይናንስ ስምምነት ፤ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የምስክር ወረቀት ፤ የመሬት አጠቃቀም ፈቃድ እና ሌሎች ከማመልከቻው ጋር ማቅረብ እንዳለበት የሚደነግግ ነው።

6. ክፍል ስድስት የኤሌክትሪክ አቅርቦትና ተያያዥነት ያላቸው ታሪፍ
    - አንቀፅ 19 ስለኤሌክትሪክ ተሸከርካሪዎች የህዝብ የሃይል መሙያ ጣቢያዎች የኤሌክትሪክ አቅርቦት ታሪፍ የሚዘረዝር ሲሆን በስሩ አምስት ንዑስ አንቀጾች የያዘ ሲሆን የኤሌክትሪክ አቅርቦት ታሪፍ በባለሥልጣኑ አዲስ የታሪፍ መደብ እስኪወጣለት ድረስ ከአጠቃላይ ታሪፍ መደብ ጋር ተመሳሳይ እንደሚሆን ፣ ኤሌክትሪክ የማከፋፈል አገልግሎት የሚሰጡ ባለፈቃዶች ለባለስልጣኑ አዲስ የታሪፍ ጥናት ሊያቀርቡ እንደሚችሉ እና የኃይል መሙያው ሂደት ሲጀምር የኃይል መሙያ ዋጋ በኤሌክትሮኒክስ ማሳያ ሰሌዳ ወይም በምልክት ሰሌዳ በኩል በግልጽ መታየት እንዳለበት የሚደነግግ ነው።
7. ክፍል ሰባት ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች
    - ከአንቀፅ 20 — 22 ያሉትን ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች የያዘ ሲሆን፣ስለአስተዳደራዊ ቅጣት ፣የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች እና መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ ይደነግጋል ።

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ የረቂቅ መመሪያዉ አስፈላጊነት ታምኖበት ተዘጋጅቶ የቀረበ በመሆኑ ታይቶ እንዲፀድቅ ቀርቧል፡፡